# ወራሽነትን ስለማጣራትና ስለ ውርስ አጣሪ

=======================

የሟች ውርስ ሟች በሞተበት ጊዜና ቦታ የሚከፈት ቢሆንም የሟች ውርስ እስከሚጣራ ድረስ የሟች ንብረት "አንድ የተለየ ንብረት፣፣ እንደሆነ ይቆጠራል። ይኸም ማለት የሟች ንብረት ከሌሎች ሰዎች ንብረት ወይም ከወራሾቹ ንብረት ጋር ሣይቀላቀል የባለቤትነት መብቱ ለወራሾች ሣይተላለፍ እንደ አንድ ልዩ ንብረት፣ Distinct estate፣ ሆኖ መያዝ እንዳለበት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 942 ይደነግጋል። ይኸም የሚሆነው ያለ ምክንያት አይደለም። የሟች ውርስ ሣይጣራ ንብረቱ ከሌሎች ሰዎች ንብረት ጋር ቢቀላቀል ውርሱን ለማስተዳደርም ሆነ ለማከፋፈል የሚያጋጥመው ችግር ከባድ በመሆኑ ነው። በመሆኑም ውርሱን የማጣራቱ ሥራ በሟች የውርስ ሰርዓት አፈጻጸም ውስጥ በቀላሉ የማይታይና እጅግ በጣም አስፈላጊ ተግባር ነው። የውርስ ማጣራት ሥራ በሟች የውርስ ሰርዓት ለማስፈፀም አስፈላጊ ተግባር ነው ካልን የውርስ ማጣራቱን ተግባር ሀላፊነት ወስዶ የሚያስፈጽም አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች መኖር አለባቸው። እነዚህ ውርሱን የማጣራት ተግባር የሚፈጽሙትን ሰዎች የውርስ አጣሪ በመባል ይታወቃሉ።

1.#ወራሽነትን ስለማጣራት

ውርስ ማጣራት ማለት፣

የሟች ወራሾች እነማን እንደሆኑ አጣርቶ መወሰን፣

የውርሱ ሀብት መጠን አይነትና ግምት እንደዚሁም የሚገኝበትን ቦታ አጣርቶ መወሰን፣

ሌሎች ሰዎች ከሟች የተበደሩትን ገንዘብ መሰብሰብና በሟች ውርስ ላይ ሊከፍላቸው የሚገቡ አስገዳጅ የሆኑ እዳዎችን አጣርቶ መክፈል፣

እንደዚሁም ሟች ልዩ የኑዛዜ ስጦታ ያደረጉላቸውን ሰዎች የተሰጣቸውን ልዩ የኑዛዜ ስጦታ መክፈል፣

ማለት እንደሆነ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 944 ድንጋጌዎች ያስረዳሉ።

እነዚህ የውርስ ማጣራት ተግባራት በብቃት እስኪከናወኑ፣ የውርሱ ንብረት እንደ ናአንድ የተለየ ንብረትን እንደሚቆጠርና ከውርሱ ሀብት ላይ ገንዘብ ለመጠየቅ መብት ያላቸው ሰዎች ማለትም የሟች አበዳሪዎች እና የፍርድ ባለመብቶች ለገንዘባቸው ዋስትናና መያዣያ የሚሆናቸው ይኸው በመጣራት ላይ ያለው የውርሱ ንብረት ነው። ይኸም በመሆኑ ውርሱ በመጣራት ላይ እያለ ከሟች ወራሾች ገንዘብ ጠያቂ የሆኑ ሰዎች በውርሱ ንብረት ላይ አንዳችም የይገባኛል ጥያቄ ማቅረብ እንደማይችሉና ምንም አይነት መብት እንደሌላቸው ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 943/1/ እና 943/3/ ድንጋጌዎች ያመለክታሉ፡፡

እነዚህ ድንጋጌዎች የራሣቸው ጠቀሜታና ግብ አላቸው። ምክንያቱም የሟች ውርስ በሚጣራበት ጊዜ የሟች ወራሾች አበዳሪዎችና ገንዘብ ጠያቂዎች የውርሱን ንብረት በመያዣያነት እንዳይዙ የሚያደርገው የሟች ወራሾች ከውርሱ ንብረት ድርሻ ሊያገኙ የሚችሉት ከሟች እዳ የተረፈ ንብረት ሲኖር ብቻ በመሆኑ ነው።

ህጉ የሟች ወራሾች አበዳሪዎች ውርሱ በመጣራት ላይ እያለ በውርሱ ንብረት ላይ የይገባኛል ጥያቄ እንዳያቀርቡ በሟች ወራሾች እዳ ምክንያት የውርሱ ንብረት በመያዣነት እንዳይያዝ የሚከለክል ነው።

እንደዚሁም ውርሱ በመጣራት ላይ እያለ ከሟች ውርስ ገንዘብ የሚጠይቁ ሰዎች ከሟች ወራሾች የግል ሀብት ላይ አንዳችም መብት እንደሌላቸው እና የሟችን የውርስ ንብረት ብቻ መከታተል እንዳለባቸው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 943 ድንጋጌዎች ያሣያሉ፡፡

እዚህ ላይ ውርስን ማጣራት አስፈላጊነት በመጀመሪያ ከሟች ገንዘብ የሚጠይቁ ሰዎች ውርሱ ከመከፋፈሉ በፊት ገንዘባቸውን እንዲያገኙ ለማድረግ፣ በማስከተልም ከውርሱ በእዳነት የሚጠየቁ ለምሣሌ ለሟች የቀብር ስነ ስርዓት የወጣው ወጭ፣ ከውርሱ መከፈል ያለበት የቀለብ እዳ እና ሟች በልዩ ኑዛዜ የሰጣቸው ስጦታዎች በቅደም ተከተል ተከፍለው ሲያበቁ ነውና ከዚህ የተረፈ ንብረት ካለ ነው የሟች የሕግ ወራሾችና ጠቅላላ የኑዛዜ ተጠቃሚዎች ከሟች ውርስ ንብረት ድርሻቸውን ያገኛሉ፡፡

በመጨረሻም የውርስ ሕጋችን ወራሾችና የኑዛዜ ስጦታ የተደረገላቸው ሰወች

ውርሱን ስለማጣራት ወይም ስለመካፈል በመካከላቸው በሚደረገው ክርክር ሁሉ አንድ ወይም ብዙ የዘመድ አስታራቂ ዳኞች እንዲያዩት ለመስማማት እንደሚችሉ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 945 ይደነግጋል።

2. #የውርስ አጣሪ

ከላይ እንደተገለፀው ውርስን ማጣራት በሟች የውርስ ሰርዓት አፈጻጸም ወቅት እጅግ በጣም አስፈላጊ ተግባር ነው። ይህንን ውርሱን የሚያጣራው ሰው ወይም ሰዎች የውርስ አጣሪ ተብለው ይጠራሉ፡ የውርስ አጣሪ ከሶስቱ በአንደኛው መንገድ ሊሾም እንደሚችል የውርስ ሕጋችን ይደነግጋል። የውርስ አጣሪ፣

በሟች ኑዛዜ መሠረት፣

በሕግ ሊመረጥ ወይም ሥልጣኑን ከሕግ ሊያገኝ፣

በዳኞች ሊሾም ይችላል።

የመጀመሪያውን በተመለከተ ሟች አንድ ኑዛዜ የተወ እንደሆነና ሟቹ በዚሁ ኑዛዜ ውስጥ የኑዛዜው አስፈጻሚ የሾመ እንደሆነ ሟች የመረጠው ሰው የውርሱ አጣሪ ሆኖ ያገለግላል። ሟች በኑዛዜ የውርስ አጣሪ የሾመ እንደሆነ ሟች በግልጽ በኑዛዜው ካላመለከተ በስተቀር በሟች ኑዛዜ ጠቅላላ የኑዛዜ ሰጦታ የተደረገለት ሰው ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ውርሱን የማጣራት መብት ይኖረዋል። ሟች የውርስ አጣሪውን በኑዛዜ የሾመ እንደሆነ ወይም ጠቅላላ የኑዛዜ ሰጦታ አድርጐ እንደሆነ ጠቅላላ ኑዛዜ ሰጦታ የተደረገለት ሰው ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ውርሱን የማጣራት መብት በቅደም ተከተል ይኖራቸዋል። ሟች የውርስ አጣሪውን በኑዛዜ የሾመ እንደሆነ ወይም ጠቅላላ የኑዛዜ ሰጦታ የተደረገለት ሰው የተገኘ እንደሆነ የሟችን ያሉ ኑዛዜ ወራሾች የውርስ አጣሪነት ስልጣን የሚያስቀረው እንደሆነ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 948 ተደንግጓል።

በሁለተኛ ደረጃ ሟች በኑዛዜ የውርስ አጣሪ ያልሾሙ እንደሆነ ወይም ሟች ጠቅላላ የኑዛዜ ሰጦታ ያደረገለት ሰው የሌለ እንደሆነ የሟች ያለ ኑዛዜ ወራሽ የሆኑ ሰዎች ሰውየው ከሞተበት ቀን አንስቶ ያለ አንዳች ፎርማሊቲ የውርስ አጣሪነት መብት እንደሚኖራቸው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 947 የሚደነግግ

ሲሆን ብዙ ሰዎች የውርስ አጣሪ በሆኑ ጊዜ የአጣሪነቱን ተግባር በመተባበር መሰራት እንዳለባቸው ወይም አንዱን በመወከል ለማሠራት እንደሚችሉ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 958 ይደነግጋል፡፡

ሶስተኛው የውርስ አጣሪ የሚሰየምበት ሰርዓት በፍርድ ቤት ውሣኔ የውርሱ አጣሪ የሚሰይምበት ሁኔታ ነው፡፡ የውርስ አጣሪ በፍርድ ቤት የሚሰየመው፣

የሟች ወራሾች የማይታወቁ እንደሆነ፣

ያለ ኑዛዜ ወራሾች ውርሱን ለማጣራት የማይፈቅዱ መሆናቸውን ገልፀው ያሣወቁ እንደሆነ፣

ሟች የኑዛዜም ሆነ ያለ ኑዛዜ ወራሽ ያልተወና የሟችን ሀብት መንግሰት የሚወርሰው በሆነ ጊዜ፣

የአሰተዳደር ሕጐችን ወይም ደንቦችን መሠረት በማድረግ ዳኞች የውርሱን አጣሪ እንደሚሰይሙ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 949 ድንጋጌዎች ያሰረዳሉ፡፡

እንደዚሁም ዳኞች በሟች ኑዛዜ፣ በሕግ ወይም በፍርድ ቤት የተሰየመውን የውርሰ አጣሪ በሌላ የውርስ አጣሪ የመተካት ሰልጣን እንዳላቸው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 951 ይደነግጋል፡፡ የውርሰ አጣሪን በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 949 መሠረት መሰየምንና በሕግ ወይም በሟች ኑዛዜ ወይም ፍርድ ቤቱ ራሱ የሰየመውን የውርሰ አጣሪ መተካት /replacement / እና substitution/ ሁለት የተለያዩ ጽንሰ ሀሣቦች ናቸው፡፡ ፍርድ ቤቱ በሕግ በሟች ኑዛዜ ወይም በፍርድ ቤቱ የተሰየመን አንድ የውርሰ አጣሪ ሰልጣንና ሀላፊነት በማንሣት ሌላ/ሌሎች/ የውርሰ አጣሪ የሚሰይመው፣

ውርሰ አጣሪው የተሾመበት ኑዛዜ ዋጋ ያለው ኑዛዜ መሆኑ አከራካሪ ሆኖ ሲገኝ ወይም፣

በሌላ ምክኒያት ውርሰ አጣሪውን በመለየት ላይ የሚያጠራጥር ነገር ሲኖር ወይም፣

ብዙ ውርሰ አጣሪዎች ለምሣሌ ሰልጣናቸው 947 የሚመነጭ ብዙ ያለ ኑዛዜ ወራሾች ኖረው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 958 በሚደነግገው መሠረት ውርሱን

በመተባበር በመግባባት ለማስተዳደርና ለማጣራት ያልተሰማሙ እንደሆነ ወይም፣ ከወራሾቹ መካከል አንዱ አካለ መጠን የላደረሰ ልጅ ወይም የተከለከለ ሰው ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት ለምሣሌ በአገር ባለመኖሩ፣ እብደቱ በግልጽ ያልታወቀ ሰው በመሆኑና በሌሎች ምክንያቶች ጥቅሙን ለማስከበር የማይችል በሆነ ጊዜ ወይም፣

የውርሱ አስተዳዳር ወይም የማጣራቱ ሰራ ልዩ ችግር ያስነሣና ልዩ ሙያ ያላቸውን ሰወች ወይም ሌላ ችግሩን ለመቅረፍ የሚችል የውርስ አጣሪ መሰየም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ወይም፣

በሕግ ሟች ኑዛዜ ወይም በዳኞች የተሰየመው አጣሪ ቸልተኛና ትጉህ ያልሆነ እንደሆነ ወይም የማጭበርበር ባህሪ የሚታይበትና ሀቀኝነት የጉደለው የሆነ እንደሆነ ወይም አጣሪው የማጣራት ሰራውን በሚገባ ለመፈፀም ችሎታ የሌለው መሆኑ የታወቀ እንደሆነ፣

ዳኞች ከማናቸውም በጉዳዩ ያገባኛል ከሚል ባለጉዳይ ጥያቄ አቅራቢነት በሕግ፣ በኑዛዜ ወይም በፍርድ ቤት ውሣኔ ተሰይሞ የነበረውን የውርስ አጣሪ በመሻር በአካባቢው ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠውን ሰው ወይም ማናቸውንም ለሰራው ብቁ ነው ብለው የሚመርጡትን ሌላ ሰው በውርስ አጣሪነት ለመሰየምና ለመተካት እንደሚችሉ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 951 ተመልክቶ እናገኘዋለን፡፡

በውርስ ህጋችን በግልጽ እንደተመለከተው በህግ፣ በሟች ኑዛዜ ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ የተመረጠ ወይም የተተካ የውርስ አጣሪ የሚከተሉት ግዴታዎችና ሀላፊነቶች ይኖሩበታል፡፡

ሟች በህይወት ዘመኑ ያደረገው ኑዛዜ ካለ ኑዛዜውን መፈለግና የሟችን የኑዛዜ ወይም ያለኑዛዜ ወራሾች እነማን እንደሆኑ ማረጋገጥ፣

የውርስ ንብረት ከብልሽትና ከብክነት ለመታደግ ተገቢውን የጥንቃቄ እርምጃ በመውሰድና ሌሎችንም አስፈላጊ ተግባራት በመፈጸም የውርሱን ሀብት ማስተዳደር፣

በግልጽ የታወቁ፣ ክርክርን የማያስነሱ መከፈል ያለባቸውን የውርስ እዳዎች

በፍትሀብሄር ህግ ቁጥር 1014 በተቀመጠው ቅደም ተከተል መሰረት መክፈል፣

ሟቹ በልዩ ኑዛዜ ያደረጋቸውን ሰጦታዎች መክፈልና የሟችን የኑዛዜ ቃል ለመፈጸምና ውጤት ለመሰጠት ማንኛውንም አስፈላጊ ጥንቃቄ ማድረግ፣

ጥያቄው ያገባኛል በሚል ማናቸውም ባለጉዳይ ሲቀርብና ዳኞችን የሚያሳምን ሆኖ ሲገኝ ሰለሰራው መልካም አፈጻጸም አንድ ዋሰ ወይም ሌላ የመልካም ሰራ አፈጻጸም ማረጋገጫ ሊሆን የሚችል መያዣ ማቅረብ፣

ሰራውን ለመተው ሲፈልግ አዲሰ አጣሪ እሰከሚሰየምና ተተክቶ ሰራውን እሰከሚጀምር ድረሰ የአጣሪነት ሰራውን የማከናወን፣

ሟች በአደረገው ኑዛዜ ሰለአጣሪነቱ የሰልጣን ወሰንና ሰለሰራው አፈጻጸም የሰጠውን መመሪያና ትእዛዝ ተከትሎ የመሰራትና ዳኞችም ሰለሰልጣኑ ወሰንና ሰለሰራው አፈጻጸም የሚሰጡትን ትእዛዞች በማክበር የአጣሪነት ሰራውን ማከናወን፣

ውርሱን አጣርቶ ከጨረሰ በኋላ ለወራሾቹ ሰለማጣራቱ የሰራ ክንውን ሪፖርት ማቅረብ፣

ውርሰ አጣሪው ማናቸውንም የህጉን ድንጋጌዎች በሟች ኑዛዜ የተሰጡትን መመሪያዎች ወይም በዳኞች የተሰጡትን ትእዛዞች በሚቃረን በጥፋቱ ወይም በቸልተኝነቱ መንገድ ለሚያደርጋቸው ጉዳዮችና በዚያ መሰረት ለሚደርሰ ጉዳት በሀላፊነት የመጠየቅ ግዴታ እንዳለበት፣

ከፍትሀብሄር ህግ ቁጥር 952፣ 954-957 እንደዚሁም የፍትሀብሄር ህግ ቁጥር 960 እና 961 በማየት መረዳት ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል ህጉ በህግ፣ በሟች ኑዛዜ ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ በውርሰ አጣሪነት ለሚሰየሙ ሰዎች ያሰቀመጠላቸው መብት አለ፡፡ ከመብቶቹ መካከል እጅግ በጣም አሰፈላጊው የውርሰ አጣሪነት ሰራ ማንም ሰው በፈቃዱ ብቻ ሊያከናውነው የሚገባና ማንም ሰው ያለፈቃዱ የአጣሪነት ሰራዎችን ለመቀበል የማይገደድ መሆኑ ነው፡፡ አንድን ተግባር አንድ ሰው ተገድዶ እንዲያከናውን ማድረግ የተከለከለና መሰረታዊ የሆነውን የሰው ልጅ ነጻነት መብት የሚነካ

በመሆኑ የውርስ አጣሪነትን ተግባር አንድ ሰው ሳይፈልግ እንዲቀበልና እንዲሰራ ማድረግ እንደማይቻል የፍትሀብሄር ህግ ቁጥር 953 በግልጽ ይደነግጋል። ሁለተኛው መብቱ ደግሞ ውርስ አጣሪው ሰራውን እፍጻሜ ለማድረስ ወይም ለተወሰነ ጊዜ ለመስራት በግልጽ ግዴታ የገባ ካልሆነ በቀር በማናቸውም ጊዜ ሰራውን መተው የሚችል መሆኑ ነው። እዚህ ላይ በጥንቃቄ መታየት ያለበት ጉዳይ ‹በግልጽ ግዴታ የገባ ካልሆነ በቀር የሚለው ሀረግ ነው። በዝምታ በህግ፣ በሟች ኑዛዜ ወይም በዳኞች የውርስ አጣሪ ሆኖ እንዲሰራ መመረጡን ተቀብሎ ሰራ መጀመሩ ብቻውን የማጣራት ሰራውን በማናቸውም ጊዜ የመተው መብቱን አያሰቀርበትም። ሰራውን የመተው መብቱ ቀሪ የሚሆነው በግልጽ እራሱን ግዴታ ያሰገባ እንደሆነ ብቻ ነው።

ሌላው እዚህ ላይ መታየት ያለበት ውርሰ አጣሪው ይህንን የማጣራቱን ሰራ የመተው መብቱን እንደፈለገው ሊጠቀምበት አይችልም። የሟች ውርሰ ንብረት የግድ መጠበቅና በጥንቃቄ መያዝ ሰለሚገባው ሌላ ተተኪ አጣሪ እሰኪመረጥና ሰራውን እሰኪረከብ ድረሰ ሰራውን እየሰራ መቆየት ያለበት መሆኑ የፍትሀብሄር ህግ ቁጥር 954 ድንጋጌዎችን በማየት ለመረዳት ይቻላል።

በሶሰተኛ ደረጃ ለውርሰ አጣሪ የተቀመጠለት መብት አጣሪው ውርሱን ለማጣራት ለሰራው ሰራ የአገልግሎት ዋጋ የማግኘት መብት ያለው መሆኑ ነው። የውርሱ አጣሪ የአገልግሎት ክፍያውን የሚያገኘው ሟች በኑዛዜው ውሰጥ በሰጠው መመሪያ ወይም ወራሾቹ በሚያደርጉት ሰምምነት ወይም ዳኞች በሚሰጡት ውሳኔ መሰረት ሊሆን እንደሚችል የፍትህ ብሄር ህግ ቁጥር 959 ይደነግጋል። በመሆኑም አጣሪው ውርሱን በማጣራት ለሰራው ሰራና ግልጋሎት ከውርሱ ንብረት ላይ ከላይ ባሰቀመጥናቸው ሁኔታዎች ሲወሰንለት የአገልግሎት ዋጋ የማግኘት መብት እንዳለው መታወቅ ይኖርበታል።

በአጠቃላይ በኢትዮጵያ የውርሰ ህግ መሰረት ውርሱን ሰለማጣራት የሚለው ጽንሰ ሀሳብ ምንነትና ይዘት እንደዚሁም ጠቀሜታ በጥንቃቄ ሊታይ የሚገባው ነው። የመጀመሪያው በምእራፍ ሁለትም ለመጠቆም እንደተሞከረው የሟች ውርሰ መከፈት እና የሟችን ውርሰ ማጣራት የሚሉት ጽንሰሀሳቦች እጅግ በጣም የተለያዩ ናቸው። የሟች ውርሰ መከፈት የምንለው ሟች ህይወቱ ካለፈበት ቅጽበት

ጀምሮ ምንም አይነት የሲቪል መብት ግዴታ ሊኖረው ስለማይችል ህጉ የሟች ህይወት ካለፈችበት ሰኮንድ ጀምሮ የሟች መብትና ግዴታ ለሟች ወራሾች ለማስተላለፍ የሚያደርጋቸውን ጥንቃቄ የሚመለከት ነው፡፡

የሟች ውርስ የሚከፈተውም ሟች መኖሪያ ሰፍራና ሟች በሞተበት ጊዜ እንደሆነ በፍትሀ ብሄር ህግ ቁጥር 826 ተመልክቷል፡፡ የሟችን ውርስ ማጣራት የምንለው ደግሞ የሟችን ያለኑዛዜና በኑዛዜ ወራሾች የሚለዩበት፣ የሟች እዳ የሚከፈልበት፣ የሟች አበዳሪዎች እና ተበዳሪዎች የሚለዩበት፣ ንብረቱ በሟች ወራሾች እስኪተላለፍና ውርሱ እስከሚዘጋበት ቀን ድረስ የንብረት ማስተዳደር ስራዎች የሚከናወንበት ውስብስብ ተግባር ነው፡፡

አሁን በሰራ ላይ ያለው የውርስ ህግ አጣሪ ስለሚሆኑ ሰዎች ሲደነግግ ቀዳሚውና የመጀመሪያው የውርስ አጣሪ የሚሆነው ሟች በኑዛዜ የውርስ አጣሪ አድርጎ የሾመው ሰው እንደሆነ ከገለጸ በኀላ ሟች በኑዛዜ የውርስ አጣሪ አድርጎ የሾመው ሰው ከሌለና በኑዛዜው የውርስ አጣሪ እንደሚሆንና ጠቅላላ ኑዛዜ የተደረገለት ሰው መገኘት የሟችን ያለኑዛዜ ወራሾች የአጣሪነት ሰራ እንደሚያስቀረው በፍትህብሄር ህግ ቁጥር 948 ንኡሰ ቁጥር 2 እና 3 የሚደነግግ ሲሆን የሟች ውርሰ መዝጋት ማለት ደግሞ የሟችን ንብረት ለወራሾች በአግባቡ የማከፋፈል ሰራን አይጨምርም፡፡

የውርሰ አጣሪው ሀላፊነት ከላይ ያነሳናቸውን ተግባር በመፈጸምና የሟችን ወራሾችና የሟች ከእዳ ተከፍሎ የሚቀረውን ንብረት በማጣራት፣ ዝርዝርና የመጨረሻ ሪፖርት ለወራሾቹ ማቅረብ ብቻ ነው፡፡ ከዚያ በኋላ የውርሱን ንብረት ማስተዳደርም ሆነ የሟችን ንብረት መከፋፈል የወራሾች መብትና ሀላፊነት እንጂ የውርሱ አጣሪ አይደለም፡፡

በመሆኑም ውርሰ አጣሪ በዋነኛነት ሊፈጽማቸው የሚችላቸው ተግባራት፣

ከሟች ውርሰ መብት አለን የሚሉትን ሰዎች ሁኔታ መወሰን፣

የሟችን የውርሰ ንብረት ማስተዳደር፣

የሟችን የውርሰ እዳ መክፈል፣ ናቸው፡፡

## ውርሰና የውርሰ ሀብት ክፍፍል

ውርሰ ማለት የአንድ በሞት የተለየን ሰው ንብረት እና ኃብት እንዲሁም ሊተላለፍ የሚችሉ መብት እና ግዴታዎች በሕይወት ላሉ አንድ እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሰዎች የሚተላለፍበት መንገድ ነው፡፡

የውርሰ ሕግ ጠቅለል ባለ አገላለፅ የሟች (አውራሽ) መብቶች እና ግዴታዎች በሕይወት ወዳሉት ወራሾቹ የሚተላለፍበት ሕግ ነው፡፡ የሟች ውርሰ መች እና እንዴት ይከፈታል፣ ወራሾች እነማን ናቸው፣ ወራሽነትን የሚያሣጡ ነገሮች ምንድን ናቸው፣ የሟች ኑዛዜ ምን ማሟላት አለበት፣ ውርሱ እንዴት እና በማን ይጣራል፣ የውርሰ ክፍያ እንዴት እና በማን ይፈፀማል እና የመሳሰሉትን የሚመራ ሕግ የውርሰ ሕግ ነው፡፡ በሃገራችን ኢትዮጵያ ይህ የውርሰ ሕግ በ1952ዓ/ም በወጣው የፍታብሄር ህጋችን በሁለተኛ መጽሃፍ በአንቀፅ አምሰት ውሰጥ ከአንቀፅ 826 እሰከ 1125 ድረሰ ተቀምጦ ይገኛል፡፡

ከላይ እንደተገለጸው ውርሰ ማለት የሟችን መብቶችን እና ግዴታዎች ወደ ሕይወት ያሉ ወራሾች ማሰተላለፍ መሆኑን ገልፀናል ፡፡ የማሰተላለፍ ሂደት የተሟላ እንዲሆን የሚከተሉት ቅደም ተከተሎች መከተል ተገኒ ነው፤

ሀ/ ውራሾችን ማጣራት ( መውረሰ የሚችሉ እነማን እነደሆኑ ማወቅ )፣

ለ/ ውርሰ ማጣራት እና

ሐ /ውርሰ ክፍፍል

ሀ/ ወራሾችን ማጣራት

ሰለ ውርሰ መክፈት

የሟች ኃብትና ንብረት እንዲሁም ወራሾች በተለያየ ቦታ ሊገኙ ሰለሚችሉ ሁሉንም በአንድ ቦታ አጠቃሎ ለማየት እንዲያመችና በውርሰ ላይ ክርክር ቢነሳ ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን ያለውን ፍርድ ቤት ለይቶ ለመወሰን እንዲቻል ውርሰ

የሚከፈተው ቦታ ተለይቶ መታወቅና በሕግም መገለፅ አለበት፡፡ በፍትሐብሔር ሕግ አንቀጽ 862/1/ ላይ እንደተገለፀው የሟች ውርስ የሚከፈተው ሟች በሞተበት ጊዜ ዋና መኖሪያው ሰፍራ በሆነበት ቦታ ነው ይላል፡፡ በመሆኑም ሟች ከመሞቱ በፊት ከአንድ በላይ የመኖሪያ ሰፍራ የነበረው ቢሆን እንኳን ውርሱ የሚከፈተው ሟች በሞተበት ጊዜ ዋና መኖሪያው በነበረው ሰፍራ ነው፡፡

በውርሰ መተላለፍ የሚችሉ መብትና ግዴታዎች

የሟች ንብረት እንዲሁም መብትና ግዴታዎቹ በውርሰ ሕግ መሠረት ለወራሾች የሚተላለፉ ናቸው፡፡ ይህ አጠቃላይ ደንብ ነው፡፡ ነገር ግን ሁሉም መብትና ግዴታዎች ሊወረሱ ወይም ለወራሾች ሊተላለፉ አይችሉም፡፡ በባሕሪያቸው አንዳንድ መብቶች እና ግዴታዎች ግለሰባዊ ናቸው፡፡ በመሆኑም በውርሰ የሚተላለፉት መብትና ግዴታዎች ከሟች መሞት ጋር አብረው ቀሪ የማይሆኑ እና መተላለፍ የሚችሉት ብቻ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ያህል ሟች የህክምና ዶክተር ቢሆን ይህን ዶክተርነቱን ለወራሾች ማውረሰ አይችለም ምክንያቱም ይህ እውቀት የግለሰቡ ብቻ በመሆኑ፡፡ እዚህ ጋር መነሳት ያለት ሌላኛው ነገር ሟች በሕይወት እያለ ይጠቀምባቸው ወይም ያገኛቸው የነበሩ ጥቅሟች በሙሉ የውርሰ አካል መሆን አይችሉም፡፡ በዚህ ሁኔታ ሊተላለፉ ከማይችሉ ጥቅሟች ውሰጥ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 827 እና 828 ላይ የተገለፁት የሕይወት ዋሰትና መድህን፣ ጡረታ እና ካሳ ናቸው፡፡ የሕይወት ዋሰትና በመድን ሰጭው እና በመድን ተቀባዩ መካከል የሚደረግ ውል ነው፡፡ በመሆኑም የሕይወት ዋሰትና መድህን ለወራሾቹ በግልጽ እነእገሌ ይጠቀሙ ወይም ለወራሾች ጥቅም የተደገ መሆኑን በግልጽ በመድን ውሉ ውሰጥ ካልተቀመጠ በሰተቀር የውርሰ ኃብት አካል አይሆንም፡፡ እንዲሁም በሞት ምክንያት ለሟች ዘመዶች ወይም ለባል ወይም ለሚሰት የሚሰጥ ጡረታ ወይ ካሳ የውርሰ ኃብት አካል አይሆንም፡፡

ወራሽ ለመሆን የሚያሰፈልጉ ችሎታ

ለወራሽነት ብቁ የሚያደርጉ በሕጉ የተቀመጡትን ቅድመ ሁኔታዎችን ሳያሟሉ እንዲሁም በሰመ ወላጅት ወይም ተወላጅነት ብቻ ወራሽ መሆን አይቻልም፡፡ ይልቁንም በሕጉ የተቀመጡትን ወራሽ ለመሆን መሟላት ያለትን/ያለባትን/ ቅድመ ሁኔታዎች ሟሟላት አለባቸው፡፡ እነዚህም ሁኔታዎች ያላሟላ ወራሽ በኑዛዜ ሰው

ቢጠቀሰም ወይም በሕግ ወራሽነቱ ቢገለፅም ከውርሱ ተጠቃሚ ሊሆን አይችልም፡፡ ለወራሽ ብቁ ለመሆን የሚያስፈልጉት ቅድመ ሁኔታዎች፡-

ሀ/ በሕይወት መኖር እና

ለ/ ለወራሽነት የማይገባ አለመሆን ናቸው፡፡

ሀ/ በሕይወት መኖር

በፍ/ብ/ሕ/ቁ 830 ላይ እንደተገለፀው አንድ ሰው ወራሽ ለመሆን አውራሹ በሚሞትበት ወቅት በሕይወት ያለ መሆን አለበት፡፡ በሌላ አገላለፅ ሟች ሲሞት ያልነበሩ ወይም ሟችን /አውራሽን / ቀድሞ የሞተ መውረስ አይችሉም፡፡ ነገር ግን በልዩ ሁኔታ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 834 ላይ እንደተገልፀው ሟች በሚሞትበት ወቅት በእናቱ ፅንሰ ውሰጥ ያለ ህፃን ተወልዶ 48 ሰዓት በሕይወት ከቆየ ውርሰ ሲከፈት እንደነበረ ተቆጥሮ የመውረሰ መብቱ ይጠበቅለታል፡፡

ለ/ ለወራሽነት የማይገባ አለመሆን

ወራሽ ለመሆን ከሚያሰፈልጉት ቅድመ ሁኔታዎች ሌላኛው ለወራሽነት የማይገባ አለመሆን ነው፡፡ አንድ ወራሽ ለወራሽነት የማይገባ የሚሆነው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 838 ላይ እንደተጠቀሰው በአውራሹ ወይም ወደ ታች የሚቆጠሩ ተወላጅ/ዎች/ ወይም ወደ ላይ የሚቀጠሩ ወላጆች ወይም ባል ወይም ሚሰት አሰቦ በመግደል የተፈረደበት ወይ ለመግደል ሙከራ የተቀጣ ወይም በሀሰት በመወንጀል ወይም በመመሰከር እንደኛውን የሞት ፍርድ ወይም ከአሰር ዓመት በበለጠ የፅኑ እሥራት ቅጣትን ለማሰከተል የሚያሰጋ ሆኖ የተቀጣ ከሆነ ነው፡፡ እነዚህን ከላይ የተገለፁትን ድርጊቶች የፈፀመ እና የተቀጣ ሰው ወራሽ መሆን አይችሉም፡፡ ነገር ግን ወራሽ የሆነው ሰው በነዚህ በተጠቀሱ ሰዎች ላይ ወንጀሉን ወይም የወንጀሉን ሙከራ ያደረገው አውራሹ ከሞተ በኃላ ከሆነ የወራሽነት መብቱን ማጣት አይፈፀምበትም፡፡

ሌላው ለወራሽነት የማይገባ የሚያደርገው ምክኒያት ሟች በነፃነት እንዳይናዘዝ ተጽእኖ ማሳደር ነው፡፡ ይህም አውራሽ ከመሞቱ በፊት ባሉት ሶሰት ወር ውሰጥ የአውራሽን ሁኔታ ከግምት አሰገብቶ ኑዛዜ እንዲይደርግ፣ እንዳይለውጥ ወይም

እንዳይሸር የከለከለ እንደሆነ ወይም እሰቦ ያለ ሟች ፍቃድ የመጨረሻውን ኑዛዜ ያበላሸ፣ እንዳይገኝ ያደረገ፣ ያጠፋ ወይም ጉዳየን በማወቅ በሐሰት ኑዛዜ የተጠቀመ እንደሆነ ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክኒያት አንድ ሰው ከጥፋቱ መጠቀም የለበትም ከሚለውን የሕግ መርህ በመነሳት ነው፡፡

ሆኖም ለወራሽነት የማይገባ የሆነ ሰው በአውራሹ (ሟች) ይቅርታ ከተደረገለት የመውረስ መብቱን ያገኛል፡፡ ይቅርታውን ማድረግ የሚችለው አውራሽ ብቻ ነው፡፡ ይቅርታውንም የሚያደርገው ግልጽ በሆነ ጽሑፍ ይቅርታ ማድረጉን ሲገልፅ ወይም በኑዛዜ የሚደረግ ውርስ ከሆነ በኑዛዜው ወራሽ ለውርስ እንደማይገባ እያወቁ ሰጦታ ካደረገለት ይቅርታ እንዳደረገለት ይቆጠራል፡፡ (የፍ/ብ/ሕ/ቁ 841)፡፡

ከጋብቻ ውጭ መወለድ ወይም የጉዲፈቻ ልጅ መሆን ለወራሽነት የማይገባ እያደርጉም፡፡ እንዲሁም የወራሽ ፆታ፣ዕድሜና ዜግነት ለወራሽነት የማይገባ እያደርጉም፡፡ ከሕጋዊ ጋብቻ የተወለደ ልጅ ሆነ የጉዲፈቻ ልጅ እድሜው፣ ፆታው እና ዜግነቱ የቱንም ይሁን የመውረስ መብት አለው፡፡

የውርስ ሥርዓቶች

በሃገራችን የውርስ ሕግ ውስጥ ሁለት አይነት የውርስ ማስተላለፊያ መንገዶች አሉ፡ እነርሱም፡-

ሀ/ ያለኑዛዜ ውርስ (INTESTATE succession) እና

ለ/ በኑዛዜ ውርስ (Testate succession)

ሀ /ያለ ኑዛዜ ውርስ (Intestate succession)

አውራሽ (ሟች) ኑዛዜ ሳያደርግ ሲሞት ወይም ያደረገው ኑዛዜ ፈራሽ በሚሆንበት ጊዜ የአውራሽ ንብረት ለወራሾች የሚከፋፈለው በሕጉ በተቀመጠው መሠረት ያለ ኑዛዜ ውርስ መሠረት ነው፡፡በዚህ ዓይነቱ ውርስ የሚካሄደው በአውራሽ ፍላጎት ሣይሆን በሕጉ መሠረት ነው፡፡ ሕጉ ደግሞ መሠረት ያደረገው የዘር ሐረግን ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክኒያት ሟች ኑዛዜ ቢያደርግ ኖሮ ለነዚህ ዘመዶቹ ሰጦታ ያደርጋል ተብሎ ስለሚገመት ነው፡፡

ያለ ኑዛዜ ውርስ ላይ የሟችን ንብረት በመጀመሪያ ደረጃ የሚወርሱት የሟች ልጆች ናቸው ።የሟች ልጆች ለመውረስ ብቁ የሚያደርጓቸውን በሕይወት ያሉ መሆን እና ለወራሽነት የማይገባ አለመሆን ቅድመ ሁኔታዎችን እስካሟሉ ድረስ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች ናቸው።በፍ/ብ/ሕ/ቁ 842(3) ላይ የሟች ልጆች ወይም ከልጆቹ አንዱ የሞተ እንደሆነ ወደታች የሚቆጠሩ ተወላጆች ትተው እንደሆነ በነሱ ምትክ ሆነው ይወርሳሉ በማለት ተገልጾአል ።የሟች ልጆች ውርሱን እያንዳንዳቸው እኩል ይካፈላሉ።

የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች ወይም የእነሱ ተወላጆች በሕይወት ከሌሉ ያለ ኑዛዜ ውርስ ወራሾች የሚሆኑት በሁለተኛ ደረጃ ዝምድና በሕጉ የተቀመጡት የሟች አባትና እናት ናቸው። በፍ/ብ/ሕ/ቁ 844(1) ላይ እንደተገለፀው የሟች አባትና እናት ውርሱን ንብረት እኩል በእኩል ይካፈላሉ። እናት ወይም እናት ወይም ሁለቱም ቀድመው የሞቱ እንደሆን የነሱን ፋንታ ወደታች የሚቆጠሩ ተወላጆቻቸው ተተክተው ይወርሳሉ። በአባት ወይም በእናት መሰመር /አንዱ መሰመር/ የሚወርሰ ከሌላ ወደ ሌላኛው መሰመር ሙሉ ውርሰ ይተላለፋል።

ያለኑዛዜ የሚደረግ ውርሰ የሟች ልጆች እና ወላጆቹ የሟች ውርሰ ሲከፈት በሕይወት ከሌሉ እና እነርሱን ተክቶ ውርሱን የሚወርሰ ሰው ከሌለ ውርሱ ወደ ሶሰተኛ ደረጃ ዝምድና ላይ ለተቀመጡ አያቶቹ ይሄዳል። ይህ በሚሆንበት ግዜ የውርሰ እኩሌታው በአባት መሰመር ላሉት አያቶች እኩሌታው ደግሞ በእናት መሰመር ላይ ላሉት አያቶች እንደሚሆን የፍ/ብ/ሐ/ቁ 845 (2) ይገልፃል። አያቶቹ ውርሰ ሲከፈት በሕይወት ከሌሉ ወደታች የሚቆጠሩ ተወላጆቻቸው ተክተዋቸው ይወርሳሉ። በአባት ወይም በእናት የትውልድ መሰመር የዘር ተከታይ ሳይኖረው የሞተ አያት ድርሻው ለዚህ መሰመር ወራሾች ይተላለፋል። አንድ የትውልድ መሥመር (የአባት ወይም የእናት) የዘር ተከታይ ሳይኖራቸው የሞቱ አያቶች ማናቸውም የውርሰ ኃብት ሁሉ ለሌላኛው ወገን የዝምድና መሥመር ወራሾች ይተላለፋል ። (የፍ/ብ/ሐ/ቀ/846)

የሟች ቅድመ አያቶች በአራተኛ ደረጃ የዝምድና የሟች ሶሰተኛ ደረጃ ዝምድና ላይ የሚገኙት አያቶች ከሌሉ እና እነርሱን ተክቶ የሚወርሰ ከሌለ ወራሽ እንደሚሆኑ በፍ/ሐ/ቁ 847 ላይ ተገልፆአል። የውርሰ እኩሌታው የአባት መሰመር ለሆኑት

ቅድመ አያቶች ወይም ተወላጆቻቸው፤ እኩሌታውን የእናት መስመር ለሆኑ ቅድመ አያቶች ወይም ትወላጆቻቸው ይሰጣል፡፡ ዘመዶች እስከ አራትኛ ደረጃ ተለይቶ ያልተገኘ እንደሆን የሟችን ንብረት ለመንግሰት እንደሚተላለፍ የ/ፍ/ሕ/ቁ 852 ላይ ተገልፆኣል፡፡

ያለ ኑዛዜ ውርሰ ላይ ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው የአባት ንብረት ወደ እናት ሐረግ እንዲሁም የእናት ንብረት ወደ አባት ሐረግ ሊተላለፍ የሚችልበትን አጋጣሚዎች እንዳሉ አይተናል፡፡ ነገር ግን በልዩ ሀኔታ ከአባት ወገን ወደ እናት ወገን ንብረት እንደማይተላለፍ በውርሰ ሕጎችን ተገልፆ ይገኛል፡፡ ይህም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 849 ላይ የጠቀመጠው የአባትን ለአባት ወገን የእናትን ለእናት ወገን መሰጠት የሚል ደንብ ነው፡፡ ይህ ደንብ ተግባራዊ እንዲሆን የሚከተሉት ቅድመሁኔታዎች መሟላት ይኖርባቸዋል ፡-

1ኛ ንብረቱ ከመጣበት መሥመር ሕጋዊ ወራሽ መኖር አለበት፣

2ኛ ሟች ሳይናዘዝ የሞተ መሆን አለበት ፣

3ኛ ንብረቱ የማይንቀሳቀሰ መሆን አለበት፣

4ኛ ንብረቱ ከአባቱ ወይም ከእናት መሥመር በውርሰ ወይም በሰጦታ የመጣ መሆን አለበት

5ኛ የሟች ተወላጆች በሕይወት የሌሉ መሆን አለባቸው፡፡

ይህም ማለት ከአባት ወገን አያቱ በሰጦታ ወይም በውርሰ የተገኘው የማይንቀሳቀሰ ንብረት የእናት ወገን ለሆነ ተወላጅ እንዳይተላለፍ እንዲሁም ከእናት በኩል የገኘው ለአባት በኩል እንዳይተላለፍ የሚያደርግ ነው፡፡ ይህም የሆነው የቤተሰብ ቅርሰ የሆነ ንብረት በቤተሰብ እጅ እንዲቀር ነው፡፡ ነገር ግን ይህን ንብረት እንዳይወርሰ የተደረገው ሰው ከንብረቱ የአላባ (usufruct) መብት አለው፡፡

ምትክነት

ከላይ እንደተገለፀው የወራሽነት መብት የተሰጠው ወራሽ ከሌለ የሱን የውርሰ ድርሻ የሱ ወራሽ በምትክነት ገብቶ እንደሚወርሰ አይተናል፡፡ ይህ የምትክነት

መርህ የሚተገበረው፡፡

1ኛ. ተተኪው ሰው ውርሱ በተከፈተበት ጊዜ ይህ የሚተካው ሰው (ወራሽ) በሕይወት የነበር መሆን አለበት

2ኛ. ምትክ ባስፈለገበት ጊዜ ይህ የሚተካው ሰው በሕይወት የሌለ መሆን አለበት

3ኛ. የሚተካው ሰው በሕይወት በነበረ ጊዜ ውርሱን ለመቀበል ፍቃደኛ የነበረ መሆን አለበት እና

4ኛ. ተተኪው ሰው ለወራሽነት ብቁ የሆነ (ለወራሽነት የማይገባ ያልሆነ) መሆን አለበት፡፡

ወራሽነትን አልፈልግም ባለ ወራሽ ምትክ ገብቶ መውረስ አይችልም፡፡ ነገር ግን ውርሱን አልፈልገውም በተባለው ሰው ምትክ ለመግባት እና ለመውረስ የሚቻል መሆኑን በፍ/ብ/ሐ/ቁ 854 ላይ ተገልፆል፡፡ ለምሳሌ፡- “ሐ  የአባቱን የ ለ ን ንብረት አልወርሰም ብሎ የወራሽነት መብቱን ቢተው አባቱን አልወርሰም ማለቱ በአባቱን ምትክ ገብቶ አያቱን  ሀ ን እንዳይወርሰ አያደርገውም፡፡ ነገር ግን ልጁ “መ  እሱን ተክቶ  ለ ን መውረሰ አይችልም፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ 856 ላይ እንደተገለፀው ከሟች ጋር የሰጋ ዝምድና የሌለው ሰው በምትክነት ገብቶ ለመውረሰ አይችልም፡፡ በሕጉ መሠረት ከሟች ጋር የዝምድና ትሰሰር የሌለው ማናኛው ሰው ተተክቶ መውረሰ አይችል፡፡

ለ/ በኑዛዜ ውርሰ (Testate succession)

ሁለተኛው ውርሰ ማሰተላለፍያ መንገድ ኑዛዜ ነው፡፡ ኑዛዜ ማለት ሟች ከመሞቱ በፊት ንብረቱን በፍላጎቱ መሠረት ለተተኪዎቹ የሚያሰተላልፍበት ሕጋዊ መንገድ ነው፡፡ ሟች በኑዛዜው ከሞተ በኋላ ሰለ ንብረት ክፍፍል፣ የልጆቹ ሞግዚት ማን እንደሚሆን፣ ንብረቱን ማን እንደሚያሰተዳድር፣ ሰለ ቀብር ሰነሰርዓቱ ሊገልፅ ይችላል፡፡ ኑዛዜ በወኪል ወይም በእንደራሴ የማይከናወን የተናዛዡ የግል ድርጊት ነው (ፍ/ብ/ሕ/ቁ/857)፡፡ ሰለዚህም ለመናዘዝ፣ ለማሻሻል ወይም ቀሪ ለማድረግ በውክልና ለሌላ አካል መሰጠት ኑዛዜውን ዋጋ ቢሰ ያደርገዋል፡፡

ኑዛዜ የሚደረገው በተናዛዡ ብቻ እንደሆን ከላይ በተገለፀው መልኩ ተረድተናል፡፡

ይሁን እንጂ ማንኛውም ሰው የሚያደርገው ኑዛዜ ሁሉ የሚፀና አይደለም። አንድ ኑዛዜ በሕግ በኩል ተቀባይነት የሚኖረው ተናዛዡ በሕግ የመናዘዝ ችሎታ ያለው ሰው ሲሆን ብቻ ነው። በሕጉ ችሎታ የላቸውም የተባሉት ሰዎች፡-

1ኛ. እድሜያቸው ከ16 ዓመት በታች የሆኑ

2ኛ. በፍርድ የተከለከሉ ሰዎች

3ኛ. የእእምሮ ሕመም ያለባቸው ሰዎች ናቸው።

አንድ እድሜው አሥራ ሰድስት ያልሞላ ልጅ ኑዛዜ ማድረግ እንደማይችል በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀፅ 295 ላይ ተገልፆል። በፍርድ የተከለከለ ሰው ከተከለከለበት እለት ጀምሮ ኑዛዜ ማድግ አይችልም። ነገር ግን ከመከልከሉ በፊት ያደረገው ኑዛዜ ተቀባይነት አለው። ይህም ሆኖ ዳኞች እንደነገሩ ሁኔታ ኑዛዜውን በሙሉ ወይም በከፊል እንዲፈርሰ የማድረግ ሥልጣን በፍ/ብ/ሕ/ቁ 368 ላይ ተሰጥቶቸዋል። የእእምሮ ሕመም ያለበት ሰው ያደረገው ኑዛዜም አይፀናም። ኑዛዜው የማይፀናው ግን ኑዛዜውን ባደረገበት ጊዜ የታወቀ ዕብድ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው።

ኑዛዜ ( Will )

ከላይ እንደተገለፀው ኑዛዜ ማለት ሟች ከመሞቱ በፊት ንብረቱን በፍላጐቱ መሠረት ለተተኪዎቹ የሚያሰተላልፍበት ሕጋዊ መንገድ ነው። እንዲሁም ኑዛዜ የሚደረገው ኑዛዜውን ለማድረግ በሕግ ችሎታ ባለው ሰው ብቻ በግሉ (በራሱ) የሚያደርገው ሕጋዊ ድርጊት ነው። ኑዛዜው የሚፀና እንዲሆን ኑዛዜውን በተመለተ መሙላት ያለባቸው ሁኔታዎች አሉ፡ እነዚህም።

1ኛ. ኑዛዜው መፈፀም የሚችል መሆን አለበት፣

2ኛ. የኑዛዜው ቃል ሕገ ወጥ መሆን የለበትም፣

3ኛ. ኑዛዜ በሃይል የተደረገ መሆን የለበትም፣

4ኛ. ኑዛዜው በመንፈስ ጫና ምክኒያት የተደረገ መሆን የለበትም

አንድ የኑዛዜ ቃል በማያሻማ መልኩ ተጠቃሚውን ወይም ጉዳዩን ካላመላከተ

ፈራሽ ነው። በማንኛውም የኑዛዜ ቃል ላይ ይህ ንብረት ለእገሌ ተብሎ በግልጽ መቀመጥ አለበት።(ፍ/ብ/ሕ/ቁ 865)። እንዲሁም አፈፃፀሙ የማይቻል ኑዛዜ ፈራሽ ነው። ለምሳሌ ሟቹ በሕይወት እያለ ሸጦ ገንዘቡን የተገለገለበትን መኪናውን አበበ የተባለ ልጄ ይውሰድ ቢል ይህ የኑዛዜ ቃል ሊፈፀም የማይችል ነው። በመሆኑም ተቀባይነት የለውም።

የኑዛዜ ቃል ሕግን ወይም መልካም ጠባይን ተቃራኒ የሆነ እንደሆነ ፈራሽ ነው። ሁልጊዜም ቢሆን የኑዛዜ ቃል ሕግን እና መልካም ጠባይን ያከበረ መሆን አለበት። ለምሳሌ ለምለም የተባለችው ልጅ አዲስ አበባ ያለውን ቤቴን የምትወስደው ጫላ የተባለውን ወዳጄን ስታገባ ነው በማለት በኑዛዜ ቃሉ አባቷ ቢገልፅ ይህ ኑዛዜ ከቤተሰብ ሕጉ ጋብቻ ተጋቢዎች ሲፈቅዱ ብቻ ነው የሚለው ስለሚቃረን ተቀባይነት የለውም።

በኃይል ተገዶ የተናዘዘ ተናዛዥ በትክክል ለሚፈልገው ሰው በፍላጐቱ መሠረት ሊናዘዝ ይችላል ተብሎ አይገመትም። ስለዚህም በኃይል ተገዶ ወይም በፍርሃት የተደረገ ኑዛዜ ፈራሽ ነው።(ፍ/ብ/ሕ/ቁ 867)

ሟች ያደረገው ኑዛዜ በከፊል ወይም በሙሉ ፈራሽ የሚሆንበት ጊዜ አለ። ይህ ሁኔታ አለ የሚባለው የመንፈስ መጫን (undue influence) ሲኖር ነው። በመሠረቱ አንድን ኑዛዜ በኑዛዜው ተጠቃሚ የሆነ ሰው ባደረገው የመንፈስ ተፅዕኖ የተደረገ ነው ብሎ ውድቅ ለማድረግ አይቻልም። በአንፃሩ ግን የሥራ ወይም የሞያ ጠባያቸው ከሟች ጋር የቀረበ ግንኙነት እንዲኖራቸው የሚያደርጋቸው ሰዎች አሉ። እነዚህ ሰዎች በተለይም ሟች ጋር ዝምድና ከሌላቸው በሥራ ወይም በሞያ ግዴታቸው ሟችን ጣዕሩ በበረታበት ጊዜ ስላገለገሉት ብቻ አለአግባብ ንብረት እንዳያገኙ ቢናዘዝላቸው ሕግ ጣልቃ ይገባል። ዕድሜው ከሀያ ዓመት በታች የሆነ ሰው ለአሳዳሪው ወይም ለሞግዚቱ ጥቅም ያደረገው ኑዛዜ ሊቀነስ ወይም ሙሉ በሙሉ ሊሻር ይችላል። ነገር ግን ሞግዚት ወይም አሳዳሪው ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆቹ ከሆኑ ግን ኑዛዜው ተፈፃሚ ይሆናል። (ፍ/ብ/ሕ/ቁ 869)።

ሟችን ከመሞቱ በፊት ባሉት ስድስት ወራት ውስጥ የሕክምና እርዳታ ሲሰጡት የነበሩ ሀኪሟች ወይም በመንፈሳዊ አገልግሎት ሲሰጡት የነበሩ የእምነት አባቶች በአገልግሎታቸው ወቅት በሟች ላይ ከፍተኛ የመንፈስ ጫናን ሊያሳድሩ ይችላሉ

ተብሎ ይገመታል፡፡ በመሆኑም ሟች በኑዛዜው ለነሱ የሰጠው ሰጦታ እንደነገሩ ሁኔታ ሊቀነሰ ወይ ሊሻር ይችላል፡፡ ነግር ግን እነዚህ ግለሰቦች ከሟች ጋር በትዳር የተሳሰሩ ወይም የሰጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ካላቸው ይህ ደኙብ ተፈፃሚ አይሆንም በማለት በፍ/ብ/ሕ/ቁ 870 ተገልጿል፡፡ በኑዛዜው ላይ ምሰክሮች ወይም አዋዋዮች ለነበሩ ሰዎች የተደረገ ኑዛዜም በተመሳሳይ ሊቀነሰ ወይም ሊሻር ይችላል፡፡

ከላይ በተገለፀው መልኩ ኑዛዜውን ለመቀነሰ ወይም ለመሻር ሥልጣን የተሰጣቸው ለዳኞች ብቻ ነው፡፡ ዳኞች በዚህ ሰልጣናቸው ለመሥራት በኑዛዜው ተጠቃሚ የሆነው ሰው ኑዛዜው እንዲፈፀምለት ጥያቄ ካቀረበበት ቀን እንሰቶ በሶሰት ወራት ውሰጥ በሕጉ መብት የተሰጣቸው ሰዎች ጥያቄ ሲቀርቡ ብቻ ነው፡፡ ዳኞች በዚህ በተሰጣቸው ሥልጣን መሠረት ኑዛዜውን በከፊል ወይም በሙሉ ሲሽሩ ከልቦና ፍርድና ከርትዕ ጋር የተሰማማ ነው የሚባሉትን ምክኒያት መግለጽ አለባቸው፡፡

ሟች የኑዛዜውን አንዳንድ ክፍሎች ሊናዘዝ የቻለው የኑዛዜው ተጠቃሚ በፈፀመው የተንኰል ወይም የማታለል ሥራ ነው በማለት የኑዛዜውን ቃል መሻር አይቻልም፡፡ ነገር ግን የኑዛዜው ቃል ላይ ሰህተት ካለ ኑዛዜው ይሻራል፡፡ ይህም የሚሆነው ተናዛዡ የፈፀመው ሰህተት ሀሳቡን ወደ አንድ አቅጣጫ እንዲያዘነብል ወሳኝ በሆነ መልኩ ተፅዕኖ ያደረገበት ለመሆኑ በኑዛዜው አነጋገር ላይ በግልጽ ሲታይ ወይም ኑዛዜውን በሚጠቅሰ በአንድ ሰነድ ላይ በማያሳጣ መልኩ ተገልፆ ሲገኝ ብቻ እንደሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 877 ተደንግጓል፡፡ አንድ የኑዛዜ ቃል ፈራሽ በሚሆንበት ጊዜ በፈራሹ ቃልና በሌሎቹ ቃላት አፈፃፀም መካከል የሚያሰተሳሰር ነገር አለ ተብሎ ካልታሰበ በሰተቀር በመርሕ ደረጃ ኑዛዜውን ሙሉ በሙሉ ፈራሽ የማድረግ ውጤት አይኖረውም፡፡

በተወሰኑ አጋጣሚዎች አንዳንድ ግለሰቦች ኑዛዜአቸውን ከአንድ መሟላት ካለት ሁኔታ ጋር አያይዘውት ይገኛሉ፡፡ ይህ ቅድመ ሁኔታ የማይቻል ወይም ለሕግ ወይም ለመልካም ፀባይ ተቃራኒ ከሆነ ግን በሕግ ፊት ተቀባይነት የለውም፡፡ (የፍ/ብ/ሕ/ቁ 879)

የኑዛዜዎች ፎረም

ኑዛዜ ሟች በሕይወት እያለ ንብረቶቹን እሱ ከሞተ በሆላ የሚጠቀሙባቸውን ሰዎች በፍላጎቱ የሚሰጥበት መሆኑን ከላጥ ተመልክተናል፡፡ ኑዛዜ የሚፈፀመው ሟች ከሞተ በሆላ በመሆኑ የሟች ፍላጎት በተገቢው እንዲፈፀም አስቀድሞ በማያሻማና ግልጽ በሆነ ፎርም መደረግ አለበት፡፡ በፍ//ብ/ህ/ቁ 880 ላይ የውርሰ ህጋችን ሶሶት ለአይነት ኑዛዜ ፎርሟችን አስቀምጧል፡፡እነሱም ፡-

ሀ/ በግልጽ የሚደረግ ኑዛዜ (public will)

ለ/ በተናዛቡ ፁሁፍ የሚደረግ ኑዛዜ (holograph will)

ሐ/ በቃል የሚደረግ ኑዛዜ (Oral will)

ሀ/ በግልጽ የሚደረግ ኑዛዜ (public will)

ይህ ዓይነቱ ኑዛዜ በጽሑፍ ሆኖ ኑዛዜው ተናዛቡ እራሱ የሚፅፈው ወይም እሱ እየተናዘዘ ሌላ ሰው የሚፅፍለት ነው፡፡ ኑዛዜው ከተፃፈ በኋላ በተናዛቡና አራት ምስክሮች ፊት ተነቦ ስለመነበቡም በኑዛዜው ውስጥ ሰፍሮ ቀኑ ተጠቅሶ ወዲያው በተናዛቡ እና በምስክሮች መፈረም አለባቸው፡፡ ይህ ካልሆነ ኑዛዜው ፈራሽ ይሆናል፡፡ በግልጽ የሚደረግ ኑዛዜ የተደረገው ለማዋዋል ሥልጣን የተሰጠው ሰው ወይም ፍርድ ቤት ፊት ከሆነ አንድ ተጨማሪ ምስክር ብቻ ነው የሚያሰፈልገው፡፡ ይህ ማለት ሁለት ምስክር ብቻ ነው የሚያሰፈልገው ማለት ነው፡፡ በዚህ መልኩ በመንግሰት ባለሰልጣናት ፊት የሚፈፀም ኑዛዜ በዕርግጥም የሟችን ነፃ ፍላጐት የሚገልጽና በትክከለኛ አዕምሮ የተሰጡ ሰለመሆናቸው በገለልተኛ አካል ለማረጋገጥ ከሚከፍቱት ልዩ ዕድል እንፃር ነው፡፡ ምክኛቱም ለማዋዋል ሥልጣን

የተሰጠው ሰው የሶሰት ምሰክሮችን ያክል ነው ተብሎ ሕጉ ግምት ሰለሚዎሰድ ነው፡፡ በኑዛዜ ላይ ምሰክር ሆነው የሚርቡ ምሰክሮች ኑዛዜው የተፃፈበትን ቋንቋ ለመሰማት ወይም ለማንበብ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡ በግልጽ የሚደረግ ኑዛዜ ሊያሟላቸው የሚገቡት ዋና ዋና ሥርዓቶች በፍትሃብሄር ሕጉ አንቀፅ 881 ሰር ተመልክተው የሚገኙ ሲሆን ኑዛዜው በምስክሮቹ ፊት መነበብ ያለበት መሆኑና ይሕ ሥርዓት ሰለመፈፀሙና የተፈፀመበትን ጊዜ የሚገልፅ ቃል በኑዛዜው ውሰጥ መካተቱ በሕጉ አሰገዳጅ ተደርገው የተቀመጡ ነጥቦች ናቸው፡፡

ለ/ በተናዛዡ ጽሑፍ የሚደረግ ኑዛዜ (holo groph will)

የዚህ ዓይነቱ ኑዛዜ በጽሑፍ ሆኖ ሙሉ በሙሉ በተናዛዡ መፃፍ አለበት፡፡ በተጨማሪም ፅሁፉ ኑዛዜ መሆኑ በግልጽ ኑዛዜ ነው ተብሎ መፃፍ አለበት፡፡ እንዲሁም በያንዳንዱ ገፅ ላይ ተናዛዡ ቀን ጽፎ መፈረም አለበት፡፡ ተናዛዡ ኑዛዜውን በኮፒውተር ወይም በታይፕ ሊፅፈው ይችላል፡፡ ነገር ግን የራሱ ኑዛዜ መሆኑን በእጅ ጽሑፍ በያንዳንዱ ገፅ ላይ መግለፅ አለት፡፡ ይህ ሁሉ ያስፈለገው ኑዛዜው የተናዛዡ መሆኑን በእርግጠኛነት ለማረጋገጥ ስለሚጠቅም ነው፡፡ ይህ ካልሆነ ኑዛዜው ፈራሽ ነው፡፡ በተናዛዡ የእጅ ጽሑፍ የሆነውን ኑዛዜ ተናዛዡ ያልተማረ መሃይም በመሆኑ ኑዛዜው የተፃፈበት ቋንቋ እና ፍችውን ማያውቀው እንደሆነ ኑዛዜው ፈራሽ ነው፡፡

ከላይ በተገለፁት ሁለቱ አይነት የኑዛዜ ፎርሟች በጋራ የሚጋሯቸው ነጥቦች አሉ፡፡ እነዚህም ሁለቱም ላይ ቀን፣ ወር እና አመተ ምህረት መፃፍ አለበት፡፡ በእለቱ በተለያዩ ምክንያቶች ይህ ተረስቶ ሳይፃፍ ቢቀር ወይም በሌላ ጊዜ ትክክለኛ ያልሆነው ሰፍሮ ቢገኝ በኑዛዜው ወይም በሌላ ሰነድ ላይ ትክክለኛውን የሚያረጋግጥ ከሆነ ኑዛዜው የፀና ኑዛዜ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ካልተረገጠ ኑዛዜ ፈራሽ ይሆናል (ፍ/ብ/ሕ/ቁ 887)፡፡

አንዳንዱ ጊዜ ኑዝዜው ላይ የሰፈረው ቃል ለመረዳት አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ ቃሉን ለመረዳት ከሌላ በሟች በራሱ የተፃፈና የተፈረመ ሰነድ ላይ አይተን እናረጋግጣለን፡፡ በኑዛዜው ቃል ላይ የሚገኘውንና መጀመሪያ የተፃፈውን ቃል የሚለውጥ ሰርዝ፣ መፋቅና ድልዝ ኑዛዜውን ፈራሽ ያደርገዋል፡፡ ምክንያቱም የተናዛዡን ፈቃድ መለወይ ስለሚሆን ነው (ፍ/ብ/ሕ/ቁ 889)፡፡ በሌላ በኩል ሰርዝ ወይም ድልዝ በመኖሩና በመፋቁ ምክንያት የኑዛዜ ቃል ፈራሽ የማይሆንበት ጊዜ አለ፡፡ ይህም እንደ ኑዛዜው ፎርም አይነት ኑዛዜው በግልጽ የተደረገ ኑዛዜ ከሆነ ምስክሮቹ ሰርዝ ድልዙን በፊርማ ያፀደቁት፤ ኑዛዜው በተናዛዡ ጽሑፍ የተደረገ ከሆነ ግለሰብ በራሱ ማስታወሻ ላይ ከገለፀ የኑዛዜው ቃል ፈራሽ አይሆንም፡፡ (ፍ/ብ/ሕ/ቁ 889)፡፡

በተወሰኑ አጋጣሚዎች ኑዛዜዎች ከአንድ በላይ በሆኑ በተለያዩ ፅሁፎች ውስጥ ሊገኙ ይችላሉ፡፡ ይህ ሲሆን በፍ/ሕ/ቁ 895 ላይ እንደተገለፀው ተቀራራቢነት

ኖሯቸው በአንድነት ሊፈፀሙ የሚችሉ ሆነው ሲገኙ በአንድነት ይፈፀማሉ፡፡ ነገር ግን በአንድ ላይ ሊፈፀሙ የማይችሉ ሲሆን በመጨረሻ የተደረገው ኑዛዜ ዋጋ ያለው ሆኖ ይፈፀማል፡፡

ሐ/ የቃል ኑዛዜ (Oral will)

የቃል ኑዛዜ በጽሑፍ ሳይሆን ተናዛዡ በቃሉ የሚደረገው ኑዛዜ ነው፡፡ የቃል ኑዛዜ አንድ ሰው የሞቱ መቃረብ ተሰምቶት የመጨረሻ ፈቃድ ቃሎቹን ለሁለት ምስክሮች የሚሰጥበት ነው፡፡ ምስክሮቹ እካለ መጠን የደረሱና በፍርድ ወይም በሕግ ያልተከለከሉ መሆን አለባቸው፡፡ በቃል በሚደረግ ኑዛዜ ተናዛዡ መናዘዝ የሚችለው ስለቀብር ሥነ-ሥርዓት በተመለከተ ትዕዛዞች መስጠት፣ ከአምስት መቶ የኢትዩጵያ ብር ያልበለጠ የንብረት ሰጦታ እና ለአካለ መጠን ላልደረሱ ልጆች አስተዳዳሪ ወይም ሞግዚት መሾምን ብቻ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 894 ላይ እንደተገለፀው በቃል ኑዛዜ ውስጥ ከላይ በተገለፁት ሌላ ማንኛውም የኑዛዜ ቃል ፈራሽ ነው፡፡ በአንድ የቃል ኑዛዜ ውስጥ ከአምስት መቶ ብር በላይ የኑዛዜ ሰጦት የተደረገ እንደሆን ከአምስት መቶ ብር በላይ የሆነው ሰጦታ ተቀናሽ ይሆናል፡፡

የኑዛዜ መሻር

የኑዛዜ ተፈፃሚነት በተዛቡ ፍላጐት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ኑዛዜ አድራጊው ሰው በፈለገው ጊዜ ኑዛዜ የማድረግ፣ የመሻር ወይም የመለወጥ መብት አለው፡፡ አንድ ተናዛዥ የተናዘዘውን ኑዛዜ ምንም አይነት ምክንያት ሳያሰፈልገው መሻር ይችላል፡፡ ተናዛዡ ይህን የሚያደርገው ኑዛዜውን ባደረገው ፎርም ነው፡፡ ይህ ማለት ኑዛዜውን ያደረገው በራሱ በተናዛዡ ጽሁፍ ከሆነ በዚያው ፎርም፤ በግልጽ በሚደረግ ኑዛዜ ከሆነ በዚያው ፎርም ኑዛዜውን መሻር ይችላል፡፡ ይህም የመሻር ሙሉ የኑዛዜ ቃሉን ወይም ደግሞ የኑዛዜውን የተወሰነ ቃል ብቻ ሊሆን ይችላል፡፡

ተናዛዡ ኑዛዜውን ለመሻር ወይም ለመለወጥ ያለውን ሀሳብ በግልጽ በሚያሳይ መልክ ኑዛዜውን በማንኛውም ጊዜ በማጥፋት፣ በመቅደድ ወይም እነጋገሩን በመሰረዝ የኑዛዜውን ቃል ለመለወጥ ይችላል፡፡ እንዲ በሚሆንበት ጊዜ ተቃራኒ የሆነ ማስረጃ ካልቀረበ በቀር ኑዛዜውን ራሱ ፈልጐ እንደሻረው ይቆጠራል፡፡ (ፍ/ሕ/ቁ 900)

## የኑዛዜ መሻር ውጤት

ኑዛዜውን ተናዛዡ በራሱ ፍላጎት ከሻረው የተናዘዘው ቃል ቀሪ ይሆናል። ይህም ማለት ተናዛዡ ኑዛዜውን በሙሉ ከሻረ ኑዛዜው ቀሪ ሆነ ማለት ነው። በከፊል የኑዛዜውን ቃል የሻረው ከሆነ ይህ የተሻረው ቃል ቀሪ ሆኖ የተቀበረው የኑዛዜ ቃል ተፈፃሚ ይሆናል። በፍ/ብ/ሕ/ቁ 901/1/ እንደተገለፀው ተቃራኒ ቃል ከሌለ በቀር ያንዱ ኑዛዜ መሻር አሰቀድሞ ተደርጐ የነበረውን ኑዛዜውን ቃል አያፀድቀውም።

## የኑዛዜ ውድቅ መሆን (Lapse of will)

የኑዛዜ ውድቅ መሆን ማለት የኑዛዜውን መፈፀም አቅም ከተናገዙ ፍቃድ ውጭ በሕግ ኑዛዜው ቀሪ የሚሆንበት ሁኔታ ነው። የኑዛዜው ውድቅ መሆን ምክንያቶች እንደየ ኑዛዜ ፎርሟች ይለያያል። በቃል የተደረገ ኑዛዜው ኑዛዜው ከተደረገ ከሶስት ወር በኋላ ተናዛዡ በሕይወት ካለ ኑዛዜው ውድቅ ይሆናል። ኑዛዜው በተናዛዡ ጽሑፍ የተደረገ ከሆነ ኑዛዜው በተደረገ በሰባት አመት ጊዜ ውስጥ ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው ሰው ወይም በፍርድ ቤት መዝገብ ቤት ዘኒድ ያልተቀመጠ እንደሆነ ውድቅ ይሆናል።

ኑዛዜው ከተደረገ በኋላ ልጅ መውለድ ኑዛዜውን ውድቅ ያደርገዋል። የተናዛዡ ባለቤት ወይም በምትክነት ፈቅዶ ለወራሽነት የቀረበ ወደታች የሚቆጠር ተወላጅ ከተወለደ ኑዛዜው ውድቅ ይሆናል። ከኑዛዜ በኋላ የተወለደን ልጅ ፈቃድ ለማግኘት በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 216 መሠረት በሞግዚቱ ወይም በንብረት አሰተዳዳሪ ተወካይነት መሆኑ ተገልጿል። ተናዛዡ ልጅ የተፀነሰ መሆኑን እያወቀ ኑዛዜውን ያደረገ እንደሆነ ወይም ተናዛዡ ጉዳዩን ቢያውቅ ኑሮ ሰጦታውን እያሰቀርም ነበር ተብሎ የሚገመት የሆነ እንደሆነ ዳኞች የኑዛዜ ሰጦታዎች በሙሉ ወይም በከፊል እንደፀኑ ለማድረግ ይችላሉ። ነገር ግን ተናዛዡ የወለደው ልጅ ወይም ወደታች የሚቆጠር ተወላጅ ቢያንስ የውርሱን ሁለት ሶሶተኛ ሁሌም (በማንኛውም ሁኔታ) ማግኘት አለበት (በፍ/ብ/ሕ/ቁ 905) ።

ሌላው ኑዛዜን ውድቅ የሚያደርገው ባል ለሚሰት በኑዛዜ ሰጦታ ሰጥቶ ወይም ሚሰት ለባሏ በኑዛዜ ሰጦታ ሰጥታ እያለ ጋብቻው ከሞተ ውጭ በሆነ ምክንያት የፈረሰ እንዲሆን ነው።

በኑዛዜ ስጦታ የተደረገለት ሰው ከሰጭው አስቀድሞ ከሞተ፣ ስጦታውን ለመቀበል ካልቻለ ወይም ደግሞ ለመቀበል ፈቃዱን ካልገለፀ የኑዛዜው ስጦታም እንደውርስ ሁሉ ውድቅ ይሆናል። ይህ ማት የኑዛዜ ስጦታ የተደረገለት ሰው ተናዛዡን ቀድሞ ከሞተ (በሕይወት ያለመሆን)፣ ለወራሽነት የማይገባ መሆን እና ኑዛዜውን ለመቀበል ፍቃደኛ አለመሆን የሰጦታ ኑዛዜውን ውድቅ ያደርገዋል።

የኑዛዜ ስጦታ የተደረገለት ሰው ከተናዛዡ በፊት ከሞተ የሱ ምትክ ሊወርሰ (ስጦታውን ሊቀበል) የሚችልበት አጋጣሚ አለ።ይህም፡-

1ኛ. ተናዛዡ ጠቅላላ ሀቡቱን የሰጠው እንደሆነ ወይም

2ኛ. ልዩ ስጦታ በሆነ ጊዜ ተቀባዩ ባለመኖሩ ሀብቱ ለመንግስት የሚተላለፍ ሲሆን ነው።

የልዩ ስጦታ ዘመዶች የሚገቡት የናዛዡ እስከ አራተኛ ደረጃ የሚቆጠር ዘመዶች ከሌሉ ብቻ ነው።

የኑዛዜ ትርጓሜ

አንዳንድ ጊዜ ኑዛዜው ግልጽ ባለመሆኑ ኑዛዜውን መረዳት በማይቻልበትና ትርጉም የሚያስፈልግበት ጊዜ አለ። እንዲህ ያለ አጋጣሚ ሲከሰት ኑዛዜው የሚተረጐመው የኑዛዜውን ዝርዝር ይዘቱን በመመርመርና ሌሎች የአካባቢ ሁኔታዎችንም በማመዛዘን የተናዛዡን ፍላጐት በመፈለግ ይሆናል። ኑዛዜ የግለሰቡ ፍላጐት ነፃ መግለጫ በመሆኑ የኑዛዜው ቃል ግልጽ ሆኖ እያለ በትርጉም አመካኘኝቶ የተናዛዡን ቃል ማዛባት ወይም ማሻሻል እንደማይቻል በሕጉ ፍ/ብ/ሕ/ቁ 910/2/ ላይ ተደንግጓል።

ይህን ጉዳይ በተመለከተ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅፅ 10 በመዝገብ ቁጥር 47487 በአመልካች አቶ ሀ/ራጉኤል ደበላ እና ተጠሪ እነ ወ/ሪት አለምፀሃይ ፈለገ መካከል በነበረው ክርክር¨ ¨ ¨ ¨ . . . በመሠረቱ ኑዛዜ ሊተረጎም የሚገባው ቃላቶቹ እና መልእክቱ ግልጽ ሳይሆን ሲቀር ነው። በሌላ አገላለፅ ኑዛዜው ግልጽ ቃላቶችንና መልዕክትን የያዘ ከሆነ ትርጓሜ መሰጠት እያስፈሌግም። ይህንን መሠረታዊ መርህን መከተል ያሉብን መሆኑን

ደግሞ የፍ/ብ/ሔ/ቁጥር 910(2) ዴንጋጌ በግልጽ ያሰገነዝባል፡፡ በመሆኑም የኑዛዜው ቃል መተርጎም ያለበት የኑዛዜው መልእክት ጥርጣሬ በሚፈጥርበት ጊዜ አሻሚ ወይም ግልጽ ያልሆነ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ይህን ደንብ ተፈጻሚ የሚሆንበትን መንገድም የፍ/ብ/ሔ/ቁጥር 910(1)፣ 911፣ 925 እና ሌሎች ድንጋጌዎች ያሳዩናል፡፡ ስለሆነም የኑዛዜው ቃልት ግልጽ የሆኑ እንደሆነ የተናዛዡ እውነተኛ፣ ትክክለኛ ፈቃድ የትኛው ነው ብሎ ትርጓሜ መሰጠትና ከኑዛዜው ቃል መራቅ የማይፈቀድ ሰለመሆኑ ከላይ የተጠቀሱት የውርሰ ሕግ ድንጋጌዎች ያሳያሉ ማለት ውሳኔ ሰጥቶል፡፡

በኑዛዜ ውስጥ የተናዛዡ የተጠቀመባቸው ቃላት አጠቃላይ ትርጉም ያላቸው ሆነው ሊገኙ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ ሀብቴን፣ ወራሾቼን፣ የማይንቀሳቀስ ንብረቴን የመሳሰሉ ቃላትን በኑዛዜው ውስጥ ተጠቅሞ ሊሆን ይችላል፡፡ በእንደዚህ ያለ ጊዜ እነዚህ ቃላት የሚረጐሙት ተዛዡ በሞተበት ወቅት የነበሩ ንብረቶች ወይም ወራሾችን ብቻ ለመግለፅ እንደተጠቀመባቸው ይቆጠራል፡፡ ነገር ግን ለዚህ ግምት ተቃራኒ የሆነ ማሰረጃ በማቅረብ ማሰረዳት ይቻላል (ፍ/ብ/ሕ/ቁ 911)፡፡

የኑዛዜ ሰጦታዎች

በኑዛዜ ተናዛዡ ለሰጦታ ተቀባዮቹ ጠቅላላ የኑዛዜ ሰጦታ ወይም ልዩ የኑዛዜ ሰጦታ ወይም ሁለቱንም በአንድ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል፡፡

ሀ/ ጠቅላላ የኑዛዜ ሰጦታ (Legalies by universal title)

ተናዛዡ ሀብቱን በጠቅላላ ወይም ከመላው ንብረቱ አንድን ክፍል በመሉ ኃብትነት ወይም በሌጣ ርሰትነት ለአንድ ወይም ለብዙ ሰዎች የሚያወርሰበት የኑዛዜ ቃል ጠቅላላ ሰጦታ ይባላል፡፡ ጠቅላላ ኃብት ሰጦታ የሚቀበለውን ሰው ሟች የሚመርጥበት የተለየ ፎርም በሕግ አልተሰጠም፡፡

ለ/ ልዩ የኑዛዜ ሰጦታ (Legalies by Singulat title)

ልዩ የኑዛዜ ሰጦታ ማለት የሚሰጡ ንብረቶችን መጠን በግልጽ የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡ ለምሳሌ አቶ ባርናባሰ ሚኒባሰ ታክሲዋን ለወንድሜ ከሁሉም ይሰጥልኝ ወይም መርካቶ ያለው ሱቄ ለእህቴ ባል ለዮናሰ ይሰጥልኝ ብሎ በኑዛዜ

ሲያስቀምጥ ይህ ልዩ የኑዛዜ ስጦታ ነው፡፡

## የጠቅላላ ኑዛዜ ስጦታ ውጤት

ተናዛዡ በኑዛዜው ላይ በግልጽ ካላስቀመጠ በቀር የሟችን ጠቅላላ ኃብት በስጦታ መልክ እንዲቀበል የተመረጠ ሰው ያለ ኑዛዜ ወራሽ (intestate succession) እንደሆነ ይቆጠራል፡፡ ይህ ሲባል የጠቅላላ ኑዛዜ ስጦታ የተደረገለት ሰው ያሉ ኑዛዜ ወራሽ ያለውን መብትና ግዴታ ይኖረዋል፡፡ ነገር ግን ተናዛዡ በግልጽ ጠቅላላ ኃብት በኑዛዜ ስጦታ ያገኘ ሰው ያለ ኑዛዜ ወራሽ እንደሆነ ሰው አይቆጠርም ሊል ይችላል፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ያለኑዛዜ ወራሾች ያላቸውን መብት እና ግዴታ አይኖረውም፡፡

## ገደብ ያለበት ኑዛዜ (conditional will)

በጠቅላላም ሆነ ልዩ የኑዛዜ ስጦታውን በኑዛዜው ሟች ይህ ሲደርስ ስጦታው ይፅናል፣ ይህ ሁኔታ ሲደርስ ደግሞ ስጦታው ይቀራል በማለት ገደብ ወይም ቅድመ ሁኔታ ሊጥል ይችላል፡፡ ለምሳሌ አቶ ሀ ሲሞት መኖሪያ ቤቱን አጐቱ ለ ሕይወቱ እስካለ ድስ ሊኖርበት ይችላል በማለት ሊናዘዝ ይችላል፡፡ እዚህ ላይ ግን “ለ ሲሞት ስጦታው ቀሪ ይሆናል፡፡

አንድ የኑዛዜ ስጦታ አድራጊ ተናዥ የኑዛዜ ስጦታ የተደረገለት ሰው በተለይ እከሌን ወይም እከሊትን እግባ ወይም አታግባ ብሎ የሚያደርገው የኑዛዜ ገደብ ዋጋ አለው በማለት የፍ/ብ/ሕ/ቁ 917 አሰቀምጧል፡፡ ነገር ግን በጠቅላላ ሁኔታ ወራሽ እንዳይገባ ወይም እንደገና እንዲያገባ የሚያስገድደው የኑዛዜ ገደብ ፈራሽ ነው፡፡ ምክንያቱም ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 34/1/ ጋር ሰለሚቃረን፡፡

ሟች ያደረገው የኑዛዜ ስጦታ አንድ ሁኔታ ሲደርስ ስጦታው ይቀራል በሚል ገደብ አድርጐበት እንደሆነ ይህ ስጦታው የሚያስቀረው ሁኔታ የደረሰ እንደሆነ የተሰጠውን ኃብት ሊመልሰ ማረጋገጫ የሚሆን ዋሰ ወይም ሌላ ዋሰትና እንዲሰጥ ባለ ጥቅም የሆነው ሰው በሚያቀርበው ጥያቄ መሠረት ዳኞች በኑዛዜ ስጦታ የተደረገለትን ሰው ሊያስገድዱ ይችላሉ፡፡

ተናዛዡ ወራሾቹን ወይም በኑዛዜ ስጦታ የተሰጣቸውን ሰዎች ከሚደርሳቸው ሐብት

ላይ በተለይ ለአንድ ወይም ለብዙ ሰዎች አንድ አገልግሎት እንዲሰጡ ግድ (ግዴታ) እንዲሆንባቸው በኑዛዜው ለመወሰን ይችላሉ በማለት በፍ/ሕ/አ 920 ላይ ተገልጿል። ነገር ግን አንድ ግዴታ የተጣለበት ወራሽ ወይም በኑዛዜ ሰጦታ የተሰጠው ሰው ስለዚህ ግዴታ አፈፃፀም በደረሰው ውርስ ወይም የኑዛዜ ሰጦታ መሠረት ካልሆነ በቀር እንደማይገደድ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 921 ላይ ተገልጿል። በፍ/ብ/ሕ/ቁ 922 ላይ ደግሞ በኑዛዜው ወይም ውርሱ የግዴታው ተጠቃሚ የሆነው ሰው የታዘዘለት እንዲፈፀምለት ለማስገደድ ይችላል። እንዲሁም ለግዴታው አፈፃፀም ዋስ ወይም ሌላ ማረጋገጫ እንዲያቀርብ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ይህኑ እንዲያደርግ ይገደዳል። ተናዛዡ ግልጽ በሆነ ሁኔታ ግዳጁን ያልፈፀመ ግለሰብ ሰጦታውን ማግኘት አይችልም የሚል ቃል በኑዛዜው ውስጥ ካላሰፈረ በስተቀር ግዳጁን አለመፈፀሙ ሰጦታውን ውደቅ እንደሚያደርገው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 923/1/ ተጠቅሷል። ተናዛዡ እንዲህ ያለ ቃል ቢያሰፈርም ግን ሰጦታን በቅን ልቦና ያገኙ ሰዎች መብት አይነካም።

ወራሹ ወይም የኑዛዜ ባለሰጦታው ለሌላው እንዲያስተላልፍ ስለመታዘዝ (Entails)

በአንድ ኑዛዜ ላይ ተናዛዡ በውርስ ወይም በሰጦታ የተሰጠውን ሐብት ወይም ከዚሁ ወስጥ የተወሰነውን ክፍል ወራሹ ወይም የኑዛዜ ባለሰጦታው ለሌለ ሰው እንዲያስተላልፍ ሊያዝ ይችላል። ይህ ግን መቼና በምን ሁኑታ መፈፀም እንዳለበት ተናዛዡ በግልጽ መጥቀስ አለት (ፍ/ብ/ሕ/ቁ 929)። ሀብቱን በመጀመሪያ የሚቀበል ወራሽ ወይም የኑዛዜ ሰጦታ ተቀባይ የሆነ ሰው ባለግዴታ ይባላል። የምትክነቱ ሥራ በሚፈፀምበት ጊዜ ከወራሽ ወይም ከኑዛዜ ሰጦታ ከተደገለት ሰው ላይ ንብረቱን የሚያገኘው ሰው ዋና ወራሽ ይባላል።

ዋናው ወራሹ ተናገዡ በሞተበት ጊዜ ውርሱን ወይም ሰጦታውን የመቀበል ችሎታ ይኑረው አይኑረው አሰፈላጊ አይደለም። ነገር ግን ውርሱን ወይም ሰጦታውን ተተክቶ በሚረከብበት ጊዜ የመቀበል ችሎታ ያለው መሆን አለበት። ባለ ግዴታው በኑዛዜ ቃል እንዲያስተላልፍ የተሰጠው ኃብት ወይም ንብረቱን በኑዛዜው ላይ የተጠቀሰው ሁኔታ ሲያጋጥም፣ የመተላለፊያው ጊዜ ሲደርስ ወይ በኑዛዜው የተጠሰው ሁኔታ ሲፈፀም የሚያስተላልፈው በመሆኑ ሊሸጠው ለሌላ 3ኛወገን

ሊያስተላልፈው ወይም በእዳ ሊያስይዘው እንዳማይችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ 931 ላይ ተገልጿል፡፡ ዳኞች ፍታህዊ ሆነው ሲያገኙት አንድን ንብረት እንዲሸጥ፣ እንዲተላለፍ የማዘዝ ሥልጣን አላቸው፡፡ ነግር ግን ወራሹ ወይም የኑዛዜ ባለሰጦታው ለሌላ ሰው እንዲያስተላልፍ የታዘዘውን የማይንቀሳቀስ ንብረት ዳኞች ከላይ በተሰጠው ሁኔታ እንዲሸጥ፣ እንዲለወጥ ወይም ለሌላ ሰው እንዳያስተላልፍ ማዘዘ እንደማይችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ 932 ላይ ተገልጿል፡፡ ይህ የሆነበት ምክኒያቱ ንብረቱ የዋና ወራሹ ስለሆነ ነው፡፡ ይህ ንብረት መብት ተጥሶ ከተገኘ በሕገ ወጥ መንገድ የተወሰደው ንብረት እንዲመለሰ ጥያቄ ማቅረብ አለበት፡፡ ዋናው ተጠቃሚ ወይም ወኪሉ ወይም ተናዛዡ የመተካቱን ሥርዓት ለማስፈፀም የመረጠው ሰው በማይገባ የተደረገ መሸጥ፣ መለወጥ ወይም መያዝ እንዲፈርሰ በማንኛውም ጊዜ ለመጠየቅ ይችላል፡፡ የመተካቱ ሥርዓት ከተደረገ በኋላ በሚከተለው ሁለት አመት ውሰጥ ክሳቸውን ማቅረብ ይችላሉ (በፍ/ብ/ሐ/ቁ 933)፡፡

ባለግዴታው ሰጦታውን ለመቀበል ካልቻለ ወይም ፈቃደኛ ካልሆነ ምንም መደረግ እንዳለበት ተናዛዡ በኑዛዜው ላይ ካልገለፀ በሰተቀር የኑዛዜ ሰጦታ የሚደርሰው ሰው ወዲያውኑ እንዲቀበል እንደሚደረግ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 935 ላይ ተገልጿል፡፡ ይህም ማለት ዋና ወራሹ እንዲወሰድ ይደረጋል፡፡ በዋና ወራሽነት መብት ያለው ሰው ቢሞትና የሚተኩትም ሰዎች ባይኖሩ ባለግዴታው ባደራ መልክ በያዘው መብትና ንብረት ያለምንም ገደቡ ሊጠቀም ይችላል፡፡ የሚተካው ሰው ባለመቅረብ ወይም እምቢ ማለት ወይም በማንኛውም ሌላ ምክንኛት በተናዛዡ ፈቃድ ካልተፈፀመ የተሰጡትን ንብረቶች ለዋናው ወራሽ ወራሾች ይተላለፋሉ፡፡ ተቃራኒ ቃል ከሌላ በቀር የተናዛዡ ወራሾች ለዋናው ወራሽ የተሰጡ ንብረቶች ላይ አንድም መብት አይኖራቸውም ሲል የፍ/ብ/ለ/ቁ 936 ይገልፃል፡፡

ከወራሽነት መንቀል (Dihersion)

አንድ ተናዛዥ ያለውን ንብረት በኑዛዜ ለማስተላለፍ ሙሉ መብት እንዳለው ያህል ንብረቱን ላለማውረሰም ሙሉ መብት አለው፡፡ በዚህ ጊዜ ተናዛዡ ወራሽ ሳያደርግ በሕግ ሊወርሱት ይችሉ የነበሩትን ግለሰቦች ወይም ከእነሱ አንድን በግልጽ ከውርሰ ውጪ ሊያደርግ ይችላላ (በፍ/ብ/ሐ/ቁ 937/1/)፡፡ ይህም ሲሆን

ከውርስ ውጪ የሆነው ወራሽ ከተናዡ በፊት እንደሞተ ተቆጥሮ ውርሱ በሕጉ መሠረት ይፈፀማል (ፍ/ብ/ሉ/ቁ 937/2/)።

አንድ ተናዛዥ ወራሾችን የመንቀል መብት ቢኖረውም ወደታች የሚቆጠሩ ተወላጆችን ጥቅም የሚጠብቅ የሕግ ድንጋጌ በውርስ ሕጋችን ውስጥ አለ። በፍ/ብ/ሕ/ቁ 938/1/ ተናዛዡ በኑዛዜው ውስጥ ከውርስ ወራሹን ለመንቀል የደረሰበትን ምክንያት ካልገለፀ በቀር ልጅን ወይም ወደታች የሚቆጠር ተወላጅን ከውርስ ቢነቅል ውኔው በሕግ እንደማይፀና ይገለፃል። ይህም ማለት ተናዛዡ ልጆቹን ወይም ወደታች የሚቆጠሩ ተወላጆችን በዝምታ መንቀል አይችልም። ነገር ግን ተቃራኒ የኑዛዜ ቃል ከሌለ በቀር የሁለተኛ፣ የሶስተኛ እና አራተኛ ደረጃ ዘመዶች እያሉ በኑዛዜው ሌላ ሰው ንብረቱን ከሰጠ እነዚህን የተጠቀሱ ዘመዶቹን ከኑዛዜው ውጭ እንዳደረጋቸው ይቆጠራል (በፍ/ብ/ሕ/ቁ 939)። ወደታች የሚቆጠሩ ተወላጆችን ተናነዛዡ በግልጽ ከኑዛዜ ውጭ ካላደረጋቸው በስተቀር የጠቅላላ ኑዛዜ ባለ ሰጦታዎች ካገኙት ንብረት ላይ እኩል ይካፈላሉ።(በፍ/ብ/ሕ/ቁ 939/1/)

ተናዛዡ ከወራሾቹ አንዱን ወይም ሁሉንም የኑዛዜውን ሙሉ ወይም አንድ ቃል ከተቃወሙ ውርሱን እንዳያገኙ ብሎ ቢናዘዝ ይህ ኑዛዜ በሕግ ፊት ተቀባይነት እንደሌላው (በፍ/ብ/ሕ/ቁ 940) ላይ ተደንግጐ ይገኛል።

ማጠቃለያ

አንድ ሰው በምድር ላይ የተወሰነ ጊዜ ከኖረ በሆላ ማለፉ የማይቀር ነው። በምድር ላይ ቆይታው ከተወለደበት ሰዓት እንስቶ እከሞተበት ጊዜ ድረስ የተለያዩ መብቶች እና ግዴታዎች አሉት። ከነዚህ መብቶቹ ውስጥ የተወሰኑት ከሞተ በሆላ ወደ ሌላ ሰው መተላለፍ የሚችሉ ናቸው። ሟች ከሞተ በሆላ ሊተላለፉ የሚችሉት መብቶቹ ለሌሎች በሕይወት ላሉ ወራሾቹ ወይም ሟች በኑዛዜ ሰጦታ ለሰጣቸው ሰዎች ይተላለፋሉ። ይህም የሚሆነው በውርስ ሕግ መሠረት ነው።

የሟችን ንብረት የሚወርሱት እነማን ናቸው፣ ወራሽነትን የሚያሳጡ ነገሮች ምንድን ናቸው፣ የሟች ንብረቶች በምን መልኩ ነው ለወራሾቹ የሚተላለፉት፣ ሟች ኑዛዜ ከተወ ኑዛዜው ሕጋዊ ውጤት እንዲኖረው ምን ምን መሟላት አለበት እና የመሳሰሉትን ነገሮች ከላይ በጽሑፍ ውስጥ ያየናቸው ናቸው።